ላትቪያ

# የእርስዎ የግል መረጃ ወደ ዩሮዳክ (EURODAC) የሚተላለፈው ለምንድን ነው?

አይነት ጂ (Type G)

**የጊዜያዊ ጥበቃ ተጠቃሚዎች**



AMHARIC

## ይህን በራሪ ወረቀት ለምን እየተቀበልኩ ነው?

በአውሮፓ ህብረት (EU) አባል አገር የጊዜያዊ ጥበቃ ተጠቃሚ ሆነው ተመዝግበዋል።

ይህ በራሪ ወረቀት በባለሥልጣናት ስለሚቀመጠው መረጃ እና ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቀመጥ ተጨማሪ መረጃ ይሰጣል።

## የጣት አሻራዬን እና ፎቶግራፌን መስጠት ያለብኝ ለምንድን ነው?

አገርዎን ለቀው ወጥተዋል እና አሁን በዚህ አገር ውስጥ የጊዜያዊ ጥበቃ ተጠቃሚ ነዎት።

የዚህ ዓይነቱ የጥበቃ ሁኔታ ጊዜያዊ ነው። የአውሮፓ ህብረት አባል አገራት ይህ ጥበቃ መቀጠል እንዳለበት ወይም እንደሌለበት በየጊዜው ይወስናሉ።

በዚህ አገር ያሉ ባለሥልጣናት የጣት አሻራዎን እና ፎቶግራፍዎን ይወስዳሉ። ይህ መረጃ፣ ከማንነትዎ መረጃ እና ከሌሎች ተዛማጅ መረጃዎች ጋር፣ ወደ ዩሮዳክ (Eurodac) የመረጃ ቋት ይተላለፋል።

ዩሮዳክ የአውሮፓ ህብረት ፕላስ (EU+) አገር ዜጎች ያልሆኑ የተወሰኑ የሰዎች ምድቦችን ልዩ የጣት አሻራ እና የፎቶግራፍ ስብስባቸው ጋር ያገናኛል።

ይህ የመረጃ ቋት መረጃዎን ማየት በሚችሉ 31 የአውሮፓ ህብረት+ አገሮች ጥቅም ላይ የሚውል ነው። የአውሮፓ ህብረት ፕላስ (EU+) አገራት በዚህ በራሪ ወረቀት መጨረሻ ላይ ተዘርዝረዋል።

**አሁን በላትቪያ ውስጥ ነዎት፣ እሱም የአውሮፓ ህብረት+ አገር ነው።**
**የአውሮፓ ህብረት+ አገሮች የሚከተሉት ናቸው፡**

27 የአውሮፓ ኅብረት (EU) አባል ሀገራት:- ኦስትሪያ፣ ቤልጂየም፣ ቡልጋሪያ፣ ክሮኤሽያ፣ ሳይፕረስ፣ ቼኪያ፣ ዴንማርክ፣ ኢስቶኒያ፣ ፊንላንድ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ግሪክ፣ ሃንጋሪ፣ ጣሊያን፣ ላቲቪያ፣ ሊቱዌኒያ፣ ሉክሰምበርግ፣ ማልታ፣ ኔዘርላንድስ፣ ፖላንድ፣ ፖርቱጋል፣ የአየርላንድ ሪፐብሊክ፣ ሮማኒያ፣ ስሎቫኪያ፣ ስሎቬንያ፣ ስፔን፣ ስዊድን እና

4 ሌሎች ሀገራት:- አይስላንድ፣ ሊችተንስታይን፣ ኖርዌይ፣ ስዊዘርላንድ።

# በዩሮዳክ (EURODAC) ውስጥ ምን መረጃ ይቀመጣል?



የሚከተለው መረጃ ሁልጊዜ ይቀመጣል፡-

- የጣት አሻራዎችዎ
- ፊትዎን የሚያሳይ ፎቶግራፍ
- አሁን የሚጠቀሙባቸው ወይም ቀደም ሲል የተጠቀሙባቸው ሁሉም ስሞችዎ
- የትውልድ ቀንዎ
- ዜግነትዎ ወይም ዜግነቶችዎ
- ጾታዎ
- የተጠቀሙባቸው የማንነት ወይም የጉዞ ሰነዶች ቅጂዎች፣ ካሉ፣ ትክክለኛነታቸውን የሚመለከት መረጃን ጨምሮ
- የጣት አሻራዎትን እና ፎቶግራፍዎን የወሰደው የባለሥልጣኑ የተጠቃሚ መለያ (user ID) እና መረጃዎ የተወሰደበትና የተላለፈበት ቀናት
- ጊዜያዊ ጥበቃ የተደረገልዎት ሰው ሆኖ የተመዘገቡበት የአውሮፓ ህብረት አባል ሀገር፣ ቦታ እና ቀን

በዩሮዳክ ውስጥ የተቀመጠ ትክክል ያልሆነ መረጃን የማግኘት እና የማስተካከል መብት አለዎት እንዲሁም መረጃዎ በህገ-ወጥ መንገድ ከተያዘ እንዲሰረዝ የመጠየቅ መብት አለዎት። ይህንን ለማድረግ የመረጃ ተቆጣጣሪውን ማግኘት ይችላሉ። የመረጃ መቆጣጠሪያው የእውቂያ ዝርዝሮች '**ስለ ዩሮዳክ (Eurodac) ማወቅ ያለብዎት**' በሚል ርዕስ ባለው በራሪ ወረቀት ውስጥ ይገኛል።

## ሌላ መረጃ በዩሮዳክ (EURODAC) ውስጥ ይቀመጣል?

የአውሮፓ ህብረት አባል አገር የጣት አሻራዎን እንዲወስድ ከተፈለገ ወይም በባህሪዎ ምክንያት ለጊዜያዊ ጥበቃ ብቁ አይደሉም ብሎ ካሰበ፣ ይህን መረጃ በዩሮዳክ (Eurodac) ውስጥ መመዝገብ አለባቸው።

ይህ የሚሆነው እርስዎን በሚመለከት የሚከተለው መረጃ ካለ ነው:-

- እንደ የጦር ወንጀል ወይም በሰብአዊነት ላይ የተፈጸሙ ወንጀሎች ያሉ በጣም ከባድ ወንጀል ፈጽመዋል
- ወደ አውሮፓ ከመምጣትዎ በፊት በሌላ አገር ከባድ ወንጀል ፈጽመዋል
- የተባበሩት መንግስታት መርሆዎች ተቃራኒ የሆነ ድርጊት ፈጽመዋል

## የእኔ የግል መረጃ በዩሮዳክ (EURODAC) ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ ይቀመጣል?



መረጃዎ የጊዜያዊ ጥበቃ ሁኔታዎ ተፈጻሚ ሆኖ እስከቀጠለ ድረስ ይቀመጣል። የጥበቃ ሁኔታዎ ካለቀ፣ መረጃዎ ይሰረዛል።

ይህ ማስታወሻ ለመረጃ አገልግሎት ብቻ የሚውል ነው። በራሱ መብቶችን ወይም ግዴታዎችን አይፈጥርም። ይህ ማስታወሻ ሊውልበት ስለሚችል ጥቅም የአውሮፓ ህብረት የጥገኝነት ድርጅትም (EUAA) ሆነ ማናቸውም በEUAA ስም የሚሰራ ማናቸውም ሰው ኃላፊነት አይወስድም።

© የአውሮፓ ህብረት የጥገኝነት ድርጅት (European Union Agency for Asylum)፣ 2025